# እድገቱ ለማነው?

## “አስደናቂ እድገት ወይንስ ተከታታይ ድህነት”

ክፍል ሶስት

**ዶር አክሎግ ቢራራ**

ድሃ፤ ኋላ ቀር፤ የእርዳታ ጥገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት የድሎት ኑሮ አሰቃቂውን የሕዝብ ኑሮ አያንፀባርቅም። የዚህ ሃተታ መሰረት የአሁኑ የእድገት ውጤት የገቢና የኃብት የተዛባ ስርጭት ከቀጠለ ለብዙ ተከታታይ ትውልዶች የተዛባ ኑሮ፤ አለመረጋጋት፤ ጥልቀት ያለው ድህነት፤ አስፈላጊ ያልሆነ የተፈጥሮ ኃብት ይገባኛልነትና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ የእርስ በርስ ግጭትና ከአሁኑ የባሰ ስደት ይፈጥራል የሚል ነው። የማንኛውም የበለፀገና በማደግ ላይ የሚገኝ አገር መንግሥት ትኩረት ለተወሰኑ ባለ ኃብቶች ተጨማሪ ገቢና ኃብት ለማበርከት አይደለም። ጥረት የሚያደርጉት በተቻለ መጠን የአብዛኛው ሕዝብ ገቢ እንዲጨምርና (ፍትህ የሚባለው)፤ የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ እንዲሻሻል ነው። ምን ማለት ነውና ለምን? በቀላል አነጋገር፤ ገቢ ጨመረ፤ ኑሮ ተሻሻለ ሲባል ዋናው መስፈርት የአብዛኛው ሕዝብ ህይወትና ኑሮ ተሻሻለ ማለት ነው። ይኼን ለማድረግ የሚቻለው **<u>የኢኮኖሚው መርህ ሕዝብን መአከል</u>** (People-centered) ያደረገ ሲሆንና **<u>ለሕዝብ ታዛዥነት ያለው የፖለቲካ አመራር</u>** (People-anchored governance) ሲኖር ነው።

ይህም ማለት፤ በቀን አንድ ምግብ የሚበላው ሶስት ምግብ ለመብላት ቻለ ማለት ነው። ለህይወት አደጋዎችን የሚያስከትል ውሃ የሚጣጣው የንጹህ ውሃ አገልግሎት አገኘ ማለት ነው። በሽታ የሚያስከትል መጸዳጃ ይጠቀም የነበረው ዘመናዊ ወይንም የተሻሻለ የመደዳጃ አገልግሎት አገኘ ማለት ነው። መጠለያው ጎጆ ወይንም የባሰ የሆነው ዘመናዊ ቤት ለመግዛት ወይንም ለመከራየት ቻለ ማለት ነው። ጤንነቱ ሲታወክ የረባ አገልግሎትና መድኃኒት ለማግኘት አቅም የሌለው ዘመናዊ የህክምና አገልግሎት አገኘ፤ አስፈላጊውን መድኃኒት ለመግዛት ቻለ ማለት ነው። ገቢው እነዚህን ለህይወት ወሳኝ የሆኑ ፍላጎቶች ካሟላ በኋላ፤ አንዳንዴም እያሟላ፤ ልጆቹን ለማስተማር ቻለ ማለት ነው። ዘመናዊ የመገናኛ አገልግሎት ለመጠቀም ቻለ ማለት ነው። ቀስ በቀስ መኪና ለመግዛት ቻለ ወዘተ ማለት ነው። ይህ ነው አንድ አገርን የማህበረሰባዊው እድገት ሰፊና ጥልቀት ያለው ነው፤ የመካከለኛው መደብ በግልጽና በሚታይ ደረጃ እየተስፋፋ ነው የሚያስብለው። በተጻራሪው ሲታይ፤ አንድን አገር አደገ የሚያስብለው ከቁንጮው ላይ ያለው ትንሽ የኃብታሞች መደብ አይደለም። ሙባረክና ቤተሰቦቹ ኃብታም ስለነበሩና በድሎት ይኖሩ ስለነበረ የግብፅ ሕዝብ የተሻሻለ ኑሮ ኖረ ማለት አይደለም። እያደጉ ሄዱ በሚባሉት ወይንም መካከለኛ ገቢ አላቸው በሚባሉት አገሮች የመካከለኛው መደብ እያደገ፤ እየሰፋና ብሄራዊ እየሆነ ስለሄደ የፍጆት እቃና አገልግሎት ፈላጊው እያደገ ይሄዳል ተብሎ በባለሞያዎች ይነገራል። ስለዚህ፤ በኢትዮጵያ እድገት አለ ማለቱ ብቻ የአገሪቱን ማህበረሰባዊ ጤናማንት አያሳይም።

ዛሬ፤ በነጻ ገበያ የሚያምኑ ሆነ በልማታዊ መንግሥት ሚና አግባብነት፤ ለሕዝብ ህይወት፤ ለሰላም፤ ለእርጋታና ለዘላቂ እድገት ተቆርቋሪ የሆኑ መሪዎች፤ የካቶሊኩን ፓፓስ፤ የአይ ኤም ኤፍን የበላይ መሪ ወዘተ ጨምሮ በተደጋጋሚ የሚያሳስባቸው **<u>ጉዳይ የገቢና የኃብት በጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች የበላይነት መያዛ</u>** ሁለት አደጋዎችን እንደሚያሳይ ነው። አንደኛው አደጋ አይ ሲስ፤ አል ሸባብ፤ አልካይዳ ለመሳሰሉ ጠብና ግጭት ጫሪ እንቅስቃሴዎች መሰረት እንደሆነና ወደፊትም በባሰ ሁኔታ እንደሚሆን። ሁለተኛው፤ የእድገት ውጤ ለጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎች ጥቅም ብቻ ከዋለ ማንኛውም አገር የማምረትና የስራ እድል የመፍጠር ኃይሉ ደካማ እንደሚሆን። ሁኔታው ስር ከሰደደ በኋላ ለመመለስ የማይቻል መሆኑንም ያሳስባሉ። ለዚህ መፍትሄ ብለው የሚያቀርቡት ሃሳብ ለሕዝብ፤ በሕዝብ የሚገዛ የፖለቲካ፤ የማህበረሰብና የኢኮኖሚ መርህ ነው።

በጥቂቶች ኪራይ ሰብሳብዎችና በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ መካከል በግልፅ እየሰፋ የሄደው የገቢ፤ የኃብትና የድሎት ኑሮ ልዩነት አደጋን እንደሚፈጠርና ድህነትን ወደማይበገር ደረጃ እንደሚያደርሰው አምናለሁ። አሁን ባለው የገቢና የኃብት ስርጭት ከቀጠለች፤ ኢትዮጵያ ወደ መካከለኛ ገቢው ክበብ ለመግባት የምትችል አይመስለኝም፤ ብትችል እደሰታለሁ። እንዲያውም የእርስ በርስ ግጭት ጥልቀት ይይዛል የሚል ስጋት አለኝ። የሌሎችን የወደቁ አገሮችን ምሳሌ አድርጌ ብወስድ፤ የተዛባ ገቢና ኑሮ ከአገዛዝ ጭካኔ ጋር አብሮ ሲከሰት ለሽብርተኞችና ለሕዝባዊ አመፅ መንስኤ ይሆናል። በአገዛዙ የተጠቀሙ ጥቂት የተያያዙ ቡድኖች የያዙትን ኃብት ለመጠበቅ ሲሉ ጭካኔ የተሞላበት፤ ለብዙ ዜጎች ህይወት እልፈት ምክንያት የሚሆን ግድያ ያካሂዳሉ። በአገዛዙ እምነት የሌላቸው ኃብታቸውን ማውጣት ይጀምራሉ (Fight or Flight). በአገር ሆኖ መታገሉ አያዋጣም የሚል ግምት ስላላቸው የሚመርጡት መሸሽን ነው። ኃብት ያለው መደበቂያ ስለማያጣ መግቢያውቸው

ብዙ ነው። መግቢያ የሌለው ተራውና ድሃው ኢትዮጵያዊ ይሆናል። አዲስ ባለኃብቶች አገራቸውን ትተው የሚሸሹበትን ምክንያት ሲሰጡ፤ ሰላምና እርጋታ ከሌለ እድገት አይኖርም፤ "ያካበትኩት ኃብት አስተማማኝ አይደለም፤ በሚል እምነት ነው። በተመሳሳይ፤ ገዢው ፓርቲ የሚናገረው እርጋታና ሰላም ከሌለ ተጠቃሚው ሕዝብ ይጎዳል ነው። የሚሸሹትም ሆነ የሚገዙት ከእድገቱ ሰላሙና እርጋታው ለማን ጥቅም እንደሚውል በግልፅ አይናገሩም፤ ሊናገሩም አይችሉም።

ዛሬ በሶሪያ፤ ቀደም ሲል በሶማሊያ እንዳየነው ሕዝብ አገሩን እየለቀቀ ልክ እንደ ጎርፍ ሌሎችን አገሮች ያጥለቀልቃል። የስራ እድል እንደተፈለገው አለመኖር፤ ከመጥፎ አገዛዝና ከእርስ በርስ ግጭት ጋር ሲጣመር ከእሳት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ይሆናል። ስደቱን ያባብሰዋል ማለቴ ነው። በቅርቡ ከአፍሪካ አገሮች ወደ አውሮፓ የሚጎርፈውን ስደተኛ ብዛትና አስጊነት አስመልክቶ የአውሮፓ ማህበር ያወጣው ዘገባ እንዲህ ይላል። In a Washington Post article dated December 17, 2015, Mohamed Yahaya of UNDP is quoted as follows. "Internal African **policies** tend to push people out," ምን አይነት ፖሊሲዎች ማለቱ ነው? "Human trafficking in places such Ethiopia and Somalia" እንደ ምሳሌ ቀርቧል። በወገኑ ጨከኖ ወገኑን ለሽያጭ ከሚያቀርብባቸው አገሮች ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች። የችግሩ መሰረት አገዛዝና የስራ እድል ማጣት ስለሆነ ስርዓቱ ካልተለወጠ የሰው ንግድ አይቆምም ማለት ነው። የጋራ ማህበሩ ያቀረበው ዘገባ ያመለከታቸው የስደትና የሰው ንግድ ምክንያቶች አሉ። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገዛዝ ዜጎቹ ተሰድው የውጭ ምንዛሬ እንዲልኩ ያደርጋል። የሚገፋው ስርዓቱ ነው፤ የሚስበው ስራና ደሞዝ ማግኘቱ ነው። "Many African governments have done little to curb migration to Europe, in part because migrant remittances can make up a significant portion of their countries's gross domestic product.....last year $11.2 billion from Europe alone."

ሌሎቹ የስደት መንስኤዎች ይጠቀሳሉ። የሰብአዊ መብቶች መገፈፋቸው፤ የእርስ በርስ ግጭቶች፤ የኃይማኖት ግጭቶች (በክርሥትናና በእስልምና ተከታዮች መካከል) ፤ የመሬት ነጠቃ፤ አለመረጋጋትና ጦርነቶች ይገኙበታል። ይኼን ግዙፍ ችግር ለመፍታት የጋራው ማህበር፤ ኢትዮጵያንና ኤርትራን ጨምሮ 23 አገሮችን **<u>የሚያካትት የ $2 billion</u>** ባጀት ፈሰስ ያለው ፕሮግራም አዘጋጅቷል። ምን ለማድረግ? በኢትዮጵያና ተመሳሳይ አገሮች የስራ እድል ለመፍጠር። የስራ እድል መፍጠሩ አግባብ አለው። ሆኖም የውጭ እርዳታ ከጥገኝነት ባሻገር ፖሊሲያዊና መዋቅራዊ ችግሮችን የፈታበት አገር አላውቅም። ችግሩ በውጭ እርዳታ ሊፈታ አይችልም። "አባይን በጭልፋ" እንደሚሉት በኢትዮጵያ **<u>ብቻ በዓመት ቢያንስ ሁለት ሚሊየን</u>** የስራ እድል መፈጠር አለበት። የግል ክፍሉ ካልፋፋና ካልተስፋፋ፤ ፓርቲውና መንግሥት ተመጣጣኝ የሆነ የስራ እድል ለመክፈት አይችሉም። በየትኛም እድገት የሚያሳይ አገር፤ **<u>90 በመቶ</u>** የሚሆነውን የስራ እድል የሚፈጥረው የግሉ ክፍል ነው። ይኼን ግዙፍ እድል የሚፈጥረው የመካከለኛውና ከፍተኛው የግል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው። የውጭ ኢንቬስተሩ አይደለም፤ አገር ተከል ወይንም አገር ወለድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ነው።

በኢትዮጵያ የወጣቱን ስደት እያባባሰው የሄደው የስራ እድል አለመኖር ብቻ አይደለም። የሰብአዊ መብቶች፤ የማህበረሰባዊ፤ የኢኮኖሚያዊና ሌሎች መብቶች መረገጥ፤ የእርስ በርስ ግጭት፤ ሁኔታውን አባብሰውታል። አፈናው ሲጨምር ስደቱም ይጨምራል። እርግጥ፤ ስደተኞቹ ተሰደው ገቢያቸው እያደገ ሲሄድና ከኑሯቸው የተረፈ ገንዘብ ሲያጠራቅሙ ለስደት ያበቃቸውን አገዛዝ ሙጥኝ ብለው አንድ ኮንዶ፤ ወይንም ቪላ ወይንም ሌላ ይገዛሉ። ኮንዶውን በመግዛታቸው ለስደት ያበቃቸውን ስርዓት ያሞግሳሉ። አንዳንዶቹ የአገራቸውን ግዛታዊ አንድነት፤ ነጻነት፤ ክብርና ሉዐላዊነት፤ የሕዝባቸውን ተፋቅሮና ተሳስቦ መኖር በኮንዶው ይለውጣሉ። አንዳንዴ "አገርን በኮንዶ ለመለወጥ ከሚቻልበት ደረጃ እንዴት ደረስን?" የሚሉ ታዛቢዎች እሰማለሁ። አገዛዙ የሚፈልገው ይኼን ነው። "ኑ! አገራችሁን አልሙ፤ ቤት ስሩ" ወዘተ እያለ ስደተኛውን ደጋፊ ለማድረግ ያላደረገው ጥረት የለም። በአንድ በኩል ስደተኛው ከአገሩ ጋር ያለው እትብት ጠንካራ ስለሆነ ኢንቩስትመንቱ አግባባ አለው ለማት ያስችላል። በሌላ በኩል በኢንቬስትሜቱ ዙሪያ የሚመጣውን ማህበረሰባዊ ቀውስና የከተማ መሬትና የቤት ግንባታ ዋጋ እየናረ መሄድ በአንክሮ አልተመለከተውም። የዜግነት መብቱን ለመጠቀም አልቻለም፤ አልደፈረም። ይኼ ሁኔታ ያስከተለው አመለካከት አለ። አንዱ፤ ለአገሩና ለመላው ሕዝብ ደህንነት የሚያስብ ለምን ጠፋ? የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ መሰማቱ ነው። ሁለተኛው፤ የፓርቲውና የስርዓቱ ባለሥልጣናት ስግብግብነት ወደ ሌላው የማህበረሰብ ክፍል፤ በተለይ ወደ ስደተኛው ተዛምቷል የሚል ነው። በእኔ ግምት፤ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት ስርዓቱ የፈጠራቸው ሁኔታዎች ናቸው። የእኔ ትውልድ የከፍተኛ ትምህርት ስደተኛ፤ ውጭ ተምሮ ወደ አገሩ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ከሁሉ በላይ የሚመኘው የተማረውን ትምህርት ለአገሩ ዘመናዊነት ለመጠቀም ነበር። አገሩ ካደገች ራሱም እንደሚጠቀም ያውቃል። መጥፎውን የውጭ ባህል ከጥሩው የመለየት ችሎታና ፍላጎት ነበረው። ሁሉን ነገር አያግበሰብስም ነበር።

ኮንዶውን ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም በላይ አምልኮ የሚኖረው ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ የማያጤነው ነገር አለ። ይኼውም፤ አገር ከሌለ፤ የእርስ በርስ እልቂት ከተካሄደ፤ ፍትህ ከሌለ ሰላም እንደማይኖር፤ ሰላም ከሌለ ኮንዶው ሊወድም እንደሚችል

ነው። አዲሱ ተጠቃሚ፤ “እድገቱ ለማነው?” የሚለውን ጥያቄ አላሰበበትም ማለት ነው። አሁን በአገራችን የተከሰተው ሁኔታ ፍትህ አለመኖሩን ያሳያል። ፍትህ ስለሌለ ስለላው ከፍተኛ ቢሆንም ሕዝቡ “ከሽፈተ” ቆይቷል። ይኼ ክፍተት አሁን ሕዝባዊ እየሆነ ሄደ እንጅ ችግሩ ከተከሰተ ቆይቷል። ተቃዋሚው ክፍል በምርጫ ዘጠና ሰባት “ለማሸነፍ” የቻለበት ዋና ምክንያት መብቶች ስለታፈኑ፤ እድሎች ስለታፈኑ፤ ጎሳዊ አድልዎ ስላየለ፤ ኪራይ ሰብሳቢነት ተቋማዊ እየሆነ ስለሄደ ነው። ሕዝቡ የአገዛዝ ስርዓት ለውጥ እንደሚፈልግ አሳይቶ ገዢው ፓርቲ የሕዝቡን ድምጽ ቀለበሰው። አሸናፊ የሆነው ተቃዋሚም ብልሃት የተሞላበት አመራር አላሳየም። አገርና ወገን ተረሳና፤ ግብግቡ የስልጣን ሆነ። ባጠቃላይ ሳየው ግን፤ ሁኔታው ታፈነ እንጅ ችግሩ አልተፈታም፤ ለእውነተኛ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ያለው ፍላጎት ከሕዝቡ እእምሮ አልወጣም። በጎንደርና በኦሮምያ የሚከፈለው መስዋእት የዚህን ፈለግ የተከተለ ነው።

በቅርቡ በጎንደርና በኦሮሚያ እንዳየነው ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የሆኑ ግዙፍ ችግሮች ገጥመዋታል። ህወሓት በበላይነት የሚያሽከረክረው ኢህአዴግ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት አላወቀውም፤ ቢያውቀውም ይክዳል። የሚቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃን የሚያንጸባርቀውም ይህንኑ ነው። የአማራ ሆነ የኦሮሞ ወይንም ሌላ ሕዝብ እንዲሁ ላምጽ ብሎ አይነሳም። ከጀርባው ቀስቃሽ ከሌለው ጎረቤት ጎረቤቱን አይገድልም። አብሮ፤ ተጋብቶ፤ ተዋልዶ፤ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ፀሎት አድርጎ፤ ቀብር ሲሆን አብሮ አልቅሶ፤ ደስታ ሲሆን አብሮ ዘፍኖ የሚኖረውን የጎንደር ሕዝብ አማራና ቅማንት ብሎ መከፋፈል በራሱ የተከሰተ አይደለም። ከጀርባው ሆኖ የጥንት ዘር፤ የጥንት ቋንቋ ወዘተ እንደ ሳይንቲስት ከመሬት ቆፍሮ ያወጣውና ወጣት ቅማንቶችን አሰልጥኖና ድጉማ ሰጥቶ ሕዝብ ከሕዝብ እንዲገዳደል ያደረገው ኃይል ህወሓት መሆኑን ብዙ ታዛቢዎች ጽፈውበታል። የእኔት እምነት አማራውና ቅማንቱ ከፋፋይን ኃይል ሲያውቅ ለራሱ የወደፊት እድልና ህይወት ሲል መተባበሩ አይቀርም። አሁንም እንደሚሰማው የቅማንትና የአማራ ጎንደሬዎች በአንድ ድምጽ “አትከፋፍሉን፤ እርስ በርሳችን አታጋጩን፤ ከእነጭራሹ ተውን፤ ችግሮቻችን ራሳችን በጋራ እንፈታለን” ወዘተ እያሉ ነው። ወንድም ከወንድሙ፤ ጎረቤት ከጎረቤቱ ጋር ሲጋጭ እርጋታና ልማት አይታሰብም እያሉ ነው። መሬታችን ለሱዳን አትስጡብን፤ ከሰጣችሁ ራሳችን መስዋእት አድርገን ዳር ድንበራችን እናስከብራለን” እያሉ ነው። ሰሚ አላገኙም። ሊያገኙም አይችሉም። ችግሩን ሆነ ብሎ የፈጠረው በከፋፍለህ ግዛው የሚያምነው ህወሓት ስለሆነ ስርዓቱ ካልተለወጠ ችግሩ አይፈታም። በአጭሩ፤ አሁን እንደምናየው ሁሉም እየተጎዳ ነው። የሁሉም ህይወት እየተናጋ ነው። በጎንደር ሆነ በኦሮሚያ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የሚነግረን ችግሩን የፈጠረው የክልሉ አመራር ስለሆነ ችግሩን መፈታት ያለበት የክልሉ አመራር ነው የሚል ተንኮል የተሞላበት ብሂል ነው። በአማራውና በኦሮሞው ክልል የበላይ ካድሬዎችን፤ የራሱን እርዮት፤ የራሱን ራእይና የራሱን ምኞት በሚያንፀባርቅ መልክ ያሰለጠነውና ድጎማ ሰጥቶ ተወላጁ ካድሬ የራሱን ወገኖች እንዲያፍን፤ እንዲገድልና እንዲያሳድድ የሚያደርገው የህወሓት ጠባብ ጎሰኛና ብሄርተኛ ቡድን መሆኑ በማስረጃዎች ተገልጿል። አዲስ ነገር አይደለም።

ብዙ ጊዜ ሲወራ የቆየው ፕሮፓጋንዳ አማራውና ኦሮሞው በማይታረቅ ጥላቻ ዑደት ውስጥ ገብቷል የሚል ነው። ይኼ የከፋፍለህ ግዛው ስልት እስካሁን ሰርቷል። ሁለቱም ክፍሎች በጋራ ሆነው በዋናው የአገዛዝ ችግር ላይ እንዳያተኩር አድርጓቸው ቆይቷል። በቅርቡ የተከሰተው ሕዝባዊ ዐመፅ የሚያሳየው እንቅስቃሴ ይኼን ለሁለቱም ግዙፍ ቁጥር ላላቸው ሕዝቦች ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ የመጠቀም ኃላፊነቱ የሁለቱም ሕዝቦች ልሂቃን፤ ምሁራን፤ ልዩ ልዩ ስብስቦችና በተለይ ወጣት ትውልድ ነው። በእኔ ግምት የአማራውና የኦሮሞው ሕዝቦች ከሚለያያቸው ይልቅ የሚያቀራርባቸው ይበልጣል። የወደፊቷን ፍትሃዊ፤ ዲሞክራሳዊ፤ እውነተኛ እኩልነት ያለባትን፤ ሁሉም ተከብሮና ከድህነት ተላቆ በሰላምና በመከባበር የሚኖርባትን ኢትዮጵያ በጋራ ተወያይተው፤ ሌላውን ሳያገሉ ለመመስረት ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። የፖለቲካ መሰረቱን፤ የወደፊትን የመንግሥት አቀራረጽ፤ አመራሩን፤ የቋንቋውንና ሌላውን ችግር ሁሉ በጋራ ለመፍታት ይችላሉ። የአሁን እድል እንዳያመልጥ ከተፈለገ የሁለቱም ክፍሎች ተቆርቋሪዎች መፈላለግ፤ መናበብ፤ መነጋገር፤ መወያየትና መደራደር መቻል አለባቸው። ይቻላል ካሉ ምንና ማን ሊያቆማቸው ይችላል?

ኢትዮጵያ ታላቅ አገር ናት፤ ጥሩና ሁሉን የሚወክል አገዛዝ ካላት ዘመናዊ የሆነ ታላቅ ህብረተሰብ ለመመስረት ትችላለች። ታላቋን አገር ታናሽ እንድትሆን ያደረግናት እኛው ልጆቿና በጎሳ የከፋፈለን አገዛዝ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በድርቅ ረሃብ በተደጋጋሚ የሚሰቃየው ዝናብ፤ ወንዝ፤ ለም መሬት፤ ለመስኖ የሚሆን ገና ያልለማ መሬትና ታታሪ ሕዝብ ስለሌላት አይደለም፤ አላት። መሰረታዊ ችግሯ የአገዛዝና የአስተዳደር መጥፎነት ነው። የድርቅ ሸነፈር እንዲሁ አይከሰትም። ተከታታይ ስደት እንዲሁ አይፈጠርም። ከድርቅ ቸነፈር ውጭ ሁሉም ስርዓት ወለድ ናቸው። ጥሩ አገዛዝ ባለባቸው አገሮች፤ ለምሳሌ ህንድና ቻይና፤ ድርቅ ቢከሰትም በቸነፈር የሚሞት ሕዝብ አይታሰብም። የማይዋጥልኝ፤ በክድህደት ዓለም የሚኖረው ህወሓት በበላይነት የሚያሽከረክረው ኢህአዴግ ተብየ መንግሥት ይኼን በግልጽ የሚታይና ለህሊና የሚቀፍ ቸነፈርና በጎንደርና በኦሮሚያ የተካሄደ ኢ-ሰብ አዊ ግፍ፤ “መብቴ ይከበር” ብሎ በተነሳው በጎንደርና በኦሮሚያ ሕዝብ ላይ ያካሂዳል። በየቀኑ ህጻናት በቸነፈር እየሞቱ አይሞቱም ይላል። ችግሩን ራሴ እወጣዋለሁ ካለ በኋላ የዓለም ለጋሶችን እርዳታ

ይጠይቃል። ይኼ በአገዛዙ በኩል ያለው ሁኔታ ሲሆን፤ ሌሎቻችንም ረሃቡን ሆነ የሕዝቡን አመጽና እልቂት በአንድነት መነጽር አናየውም።

አብረውና ተባብረው መስራት የሚገባቸው ተቃዋሚዎች ተፈላልገው በብልሃት አንድ ላይ ስላልቆሙ አሁንም ወገኖቻችን በተናጠል እየሞቱ፤ እየታሰሩ፤ እየተሰደዱ፤ በቸነፈር እየተጎዱ ነው። በአንድነት ድምፅ አይሰማም የምልበትን ምክንያት በምሳሌ ላቅርበው። በጎንደር በእስር ቤት የታጎሩ እዚያው እንዲቃጠሉ፤ ለመሸሽ የሞከሩት የጥይት በረዶ እንዲርከፈከፍባቸው መደረጉና በኦሮሚያ የስምንት ዓመት ወጣት ሳይቀር መገደሉ የአረመኔነት አገዛዝ ምሳሌ ነው። ወንድማማቹን የቅማንቱንና የአማራውን ሕዝብ እንዲገዳደል ማድረግ ጭካኔና አረመኔነት ነው። በሰላም የሚኖረውን አማራ ከቀዩ ማባረር፤ መግደል፤ ማሳደድና ማዋረድ አረመኔነት ነው። በጎንደር ከተማ ኢትዮጵያዊያን በእስር ቤት ቃጠሎ ሲሞቱ ፈጥኖ አለመድረስና ይበላቸው ማለት የአረመኔነት ምሳሌ ነው። ብዙ ሽህ የኦሮሞ ወጣቶችን ሰላማዊ ሰልፍ ስላደረጉ በፀረ-ሽብርተኛነት አሳቦ  በገፍ ማሰር ጭካኔ ነው። ገዢው ፓርቲ ያወገዘው የነበረውን የደርግ ጭካኔ በባሰ ሁኔታ እየቀጠለበት ከሄደ እርጋታና ሰላም አይኖርም። በተመሳሳይ፤ ከህብረተሰቡ አንጻር ስመለከተው፤ እንደዚህ ያሉ ጭካኔዎች የተለመዱ መሆናቸው ራሳችንንም ወደ የህሊና ጥያቄ ውስጥ አስገብተውናል። መቸ ነው፤ በተናጠል ሳይሆን በጋራ አንዱ ወገናችን ለሌላውን ደግፎ የሚነሳው? ሌላውን ደግፎ የሚሞተው? መቸ ነው ኦሮሞውም፤ ጎንደሬውም፤ አፏኩም፤ ሶማሌውም በጋራ ሆኖ አባቴ፤ እናቴ፤ ወንድሜ፤ እህቴ፤ አክስቴ ወይንም አጎቴ እያልን በጋራ የምንነሳበት? በየትኛውም አገር፤ የተለያየና ለመስማማት ያልቻለ ሕዝብ በቀላሉ ይመታል። የተለያየ የህዝብ ዐመጽ በቀላሉ ይወድቃል። በውጭ የምንኖረው "ተቃዋሚ **ነን" ባዮች በጋራ ሆነን አቤቱታና ድምፅ ያሰማንበት ጊዜ የለም።**

**ፍትህ የጋራ ነው**

በእኔ ስሌት፤ ባለመተባበር ምክንያት ሕዝቡ የሚከፍለው ዋጋ ከፍተኛና አደገኛ ነው። ሌላም ጉዳይ አለ። በእኛ ቸልተኛነትና መከፋፈል ምክንያት ለኢትዮጵያ መፈራረስ ትኩረትና ድጋፍ ለሚሰጡ የውጭ ኃይሎች ወንፊት አበርክተናል። ባህሪያችን፤ ጭፍን፤ ግትርና ግለሰባዊ መሆኑ እየጎዳን ነው። ልንክደው የማንችለው ሃቅ አለ። ይኼውም የፖለቲካ ባህላችን ብሄራዊ ችግሮችን በውይይትና በድርድር ለመፍታት የሚያስችል ፈቃደኛነትን፤ መተማመንን፤ ችግሮችን በመነጋገር ለመፍታት መወሰንን  ይጠይቃል። ይኬ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የጉራጌ፤ የትግሬ ወይንም ሌላ ሕዝብ ወይንም ልሂቃን ጥያቄ አይደለም። ሁላችንም የምንመኛቸውና የምንጋራቸው የአገዛዝ ሁኔታዎች አሉ--በሕግ ፊት የሁሉም ኢትዮጵያዊያን እኩልነት፤ ሰብአዊ መብቶች፤ ድምጽ፤ ተሳትፎና ተወካይነት መከበር፤ የሁሉም ጎሳዎች ባህሎች፤ ታሪኮች፤ ልምዶች፤ ጥቅሞች፤ ቋንቋዎችና ሌሎች ኃብቶች መከበር፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ኃይማኖቶች መከበር፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን በማንኛውም ክልል በክብርና በደህንነት የመኖር መብት መከበር፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚሳተፉበት ነጻና ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ ተካሂዶ ሕዝብ ድምፅ የሰጠበትና የተሳፈበት ዲሞክራሳዊ መንግሥት እንዲቋቋም የህብረት ስራ ማካሄድ የሚሉት በሁሉም ተቃዋሚ ክፍሎች ይነገራሉ። በእነዚህ የምንስማማ ከሆነ ተፈላልገን በአንድ ላይ ሆነን ለመወያየትና ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ አማራጭ ለመስጠት የማንችልበት መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? ከጎሳና ከኃይማኖት በላይ አስበን ይኼን ጥያቄ የመመለስ ታሪካዊ ግዴታ አለብን። ከላይ የአማራውንና የኦሮሞውን መተባበር አስፈላጊነት አስመልክቸ እንዳቀርብኩት፤ ሌላው የወደፊት ስርዓት ጉዳይ በውይይት፤ በንግግር፤ በመተማመን፤ በድርድር ይፈታል። ይኼን ታሪካዊ ጥሪ ለመመለስ የሚችሉ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የጉራጌ፤ የደቡብ፤ የአፋር፤ የአፏክ፤ የሶማሌ፤ የትግሬ ወዘተ ልሂቃን፤ ምሁራን፤ ሽማግሌዎችና አባቶች እንዳሉ አምናለሁ። ሕዝቡ የሚፈለገው መግባባትን ነው። ገዢው ፓርቲ ህዝብን ከሕዝብ የከፋፈለ መሆኑን አብዝኛው ተቃዋሚ ይቀበላል። ስለሆነም፤ ገዢውን ፓርቲ ብቻ መሰናከልና ማነቅ ማድረግ አግባብ የለውም። መጀመሪያ የተቃዋሚው ክፍል ስራውን ይስራ እላለሁ፡፡ የገዢውን ፓርቲ ፈቃድ የምንጠብቅ ከሆነ ችግሩ በምንም አይፈታም። ለምን?

ገዢው ፓርቲ የረባ ተቃዋሚ እንዳለ አይቀበልም። ከማፈን ባሻገር ሁሉንም እየለቀመና እየለያየ አፈራርሷቸዋል። ህብረት እንዲፈጥሩ አይፈልግም። ስልጣኑን ለመልቀቅ አይፈልግም። ትእቢተኛና ትምክኽተኛ የሆነ አገዛዝ ሁል ጊዜ የሚመካው በውይይትና በመደራደር ሳይሆን በመሳሪያ ኃይል ነው። በጀርባ ሆኖ ሕዝቡ የውስጥ ችግሩን እንዲፈታ የሚቀሰቅሰው በግጭት፤ በቂም በቀል፤ አንዱ ሌላውን እንዲፈራው በማድረግ ነው። የተቃዋሚው ክፍል ማድረግ ያለበት ለመላው ሕዝብ መብትና የኑሮ መሻሻል ተባብሮ መስራት ነው። ማመን ያለበት የፖለቲካ ብልሃት፤ ሕዝብ ካመረረና በጋራ ከተነሳ ማንም ኃይል የማቆመው መሆኑን ነው። ውጣ ውረዱና የሚከፈለው መስዋእት ከፍተኛ ቢሆንም በሕዝብ እምነት ያለው ቡድን ያሸንፋል። ህወሓት/ኢህአዴግ ከሚያወግዘው ከደርግ አገዛዝ የተማረው አንድም ነገር የሌለ መሆኑን ማስትጋባት አግባብ አለው። ካለፉት ከወደቁ አምባገነኖች ሊማር ቢችል ኖሮ ሕዝብ የጠላው አገዛዝ ንጹህ ዜጎችን ቢገድል፤ ቢያስር፤ ቢደበድብ፤ ቢያቆስል፤ ቢያሳድድ የተባበረን የሕዝብ አመፅ ሊቋቋም አይችልም የሚለውን ሁኔታ አይረሳውም ነበር። የደርግ አምባገነን አገዛዝ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የጦር ኃይል ነበረው። የግብጹ ሞባረክ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ተወዳዳር

የሌለው የስለላ መረብ፤ የጦርና የፖሊስ ኃይል፤ ግዙፍ ኃብት ነበረው ወዘተ። እነዚህ አምባገነኖች በተባበረ ሕዝባዊ አመጽ ወድቀዋል። የአሁኑ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከእነዚህ የተለየ አይደለም። ሆኖም፤ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ክፍሎች ህወሓት በፈጠረላቸው የጎሳና የኃይማንት መከፋፈልና የእርስ በርስ ውድድር አጀንዳ ተበክለዋል። የገዢውን ፓርቲ አጀንዳ ይዞ መጓዝ ምን ትርጉም አለው ብሎ መጠየቅ ብልሃት ነው። የተቃዋሚው ትኩረት ከፋፍሎ ከሚቀጠቅጠውና ከሚያያፍነው ገዢ ፓርቲ ላይ ቢሆን ኖሮ ዲሞክራሳዊ ለውጥ ይቻል ነበር። የኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ባህል፤ ማለትም የተቃዋሚ ተቃዋሚ መሆኑ ካልቆመ አፈናው፤ ግድያው፤ ማሰሩና ማሳደዱ ይቀጥላል።

በጎንደር ሕዝብ ላይ የተካሄደውና አሁንም የሚካሄደው የግድያ፤ የአፈና፤ የማሳደድ ወዘተ ግፍ፤ በወጣት የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የሚካሄደው ግድያ፤ አፈና፤ ማሳደድ ወዘተ የሚያሳየን ተመሳሳይ ሁኔታ አለ። ይኼውም የህወሓት አባቶችና ተተኪዎች ከቡድናቸው ጥቅምና ደህነነት ውጭ ለሌላው ኢትዮጵያዊ ህይወት፤ ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ለሰብአዊ ክብርና ኑሮ ደንታ እንደሌላቸው በተከታታይ አይተናል። በቅርቡ በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር የድንበሩን ጉዳይ አስመልክቶ የተናገረው አግባብ አለው። "የድንበሩ ችግር አሁን የተነሳ ሳይሆን የቆየ ነው….አስቸጋሪ የሆነብን ከስልጣኑ የተወገደውን ጎሳ የሚወክለው የአማራው ክልል ነው። አገሪቱን የሚገዛው በካርቱም "ማህፀን የተወለደው" የትግራይ ጎሳ ነው---" ወዘተ ብሏል። የተቃዋሚው ክፍል ራሱንና ገዢውን ፓርቲ መጠየቅ ያለበት፤ አምባሳደሩ ይኼን ሲል ሁለት መንግሥታት አሉ ማለቱ ነው? ኢትዮጵያ በጎሳ ስለተከፋፈለች እድሉን ህወሓት ስለሰጠን ተከታታይ መንግሥታት ያልተቀበሉትን ድንበር ለእኛ ይሰጥ ማለቱ ነው? አምባሳደሩ ጉዳዩ አስቸኳይ አይደለም ብሎ እየተናገረ ህወሓት የግዌንን መስመር ህጋዊ ለማድረግ ምን አስቸኮለው? ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማሪያም አንድም ሜትር መሬት የማይሰጥ ከሆነ ለምን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል አይገባም? ኢትዮጵያና ሱዳን የሚፈራረሙት የድንበት ውል ምን እንደሆነ ለምን ለሕዝብ ይፋ አያደርግም? በድንበሩ ዙሪያ የተቃዋሚው ክፍል አሁንም የተሳሳተ መረጃ ይከተላል። ለሱዳን የሚሰጠው ግዙፍ መሬት ኤርትራን ከሚያዋስነው የኢትዮጵያ ድንበር ጀምሮ እስከ ደቡብ ሱዳን እርዝመቱ 1,600 ኪሎሜትር፤ ስፋቱ ከ20-60 ኪሎሜትር የሚደርስ፤ ጎንደርን፤ ጎጃምን፤ ወለጋን፤ ከፋን፤ ጋሙ ጎፋንና ጋምቤላን የሚመለከት ለም መሬት ነው። ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ይመለከታል። ለኢትዮጵያ የወደፊት ደህንነት ጠንቅ ይሆናል። ኢትዮጵያ ወንዞቿን እንዳትጠቀም መሰናክል ይፈጥራል ወዘተ። ይኼም ራሱ የወቅቱ አንገብጋቢች የሆነ የጋራ ችግር ነው።

ቦጎንደርም ሆነ በኦሮሚያ ገዢው ፓርቲ የክልሉን ደጋፊዎች፤ ፖሊሶችና ሌሎች እየተጠቀመ ዛሬ አንዱን ጎሳ፤ ነገ ሌላውን፤ ዛሬ አንዱን ኃይማኖት፤ ነገ ሌላውን ሲገድልና ሲያሳድድ ቆይቷል። ከዚህ በፊት በአኟኮች፤ በኦጋዴን ሶማሌዎች፤ በአማራ ብሄረሰብ አባላት ላይ በተደጋጋሚ የተካሄደው ግድያ በወንጀለኛነት የሚያስከስስ ነው። ሆኖም፤ ሁሉም ኢትዮጵዊያን ድምፅ ለማሰማት ፈቃደኛ አልነበሩም። "ጨኸት በተናጠል፤ ለቅሶ በተናጠል፤ ትግል በተናጠል" የት እንደሚያደርሰን አላውቅም። ህወሓት ይኼን ተከታታይ የመከፋፈል ባህርይ ለመብቱ የሚነሳውን ሁሉ ለመቅጣት መሳሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል። የሱዳኑ አምባሳደር የተናገረውን ስመረምር የሚናገረው የህወሓትን ቋንቋ ነው። ከከፋፍለህ ግዛውን ቋንቋ አሁንም እየተጠቀመበት ነው። በጋምቤላ፤ በኦጋዴን፤ በጎንደር፤ በኦሮሚያና በሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች ፊት ለፊት ሆነው ወገኖቻቸውን የሚድገሉ፤ የሚያስሩ፤ የሚደበድቡ የአካባቢው ደምዝተኞች ናቸው። ችግሩ ከእነሱ አቅም በላይ ሲሆን የፌደራሉ ኃይል ይላካል። የህወሓት አባላት ባይሆኑም የህወሓትን መርህ የተቀበሉ አዲስ ተጠቃሚዎችና አዲስ ህወሓቶች አሉ ማለት ነው። የበላይ አዛዡና ተቆጣጣሪው ህወሓት እንዳለ ሆኖ፤ የኢህአዴግ አባላት ቁጥር ከስድስት እስከ ሰባት ሚሊየን ይገመታል ሲባል ሁሉንም የጎሳ ፓርቲዎች ለመሰብሰብ ሞክሯል ማለት ነው። ዋናዎቹ  የእድገት ተጠቃሚዎች የህወሓት አባላት፤ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይኼን ማለት ግን ሌሎች የፓርቲና የመንግሥት ኪራይ ሰብሳቢዎችና ሙሰኞች የሉም ማለት አይደለም። ጎንደርም አሉ፤ ኦሮሚያም አሉ፤ ጋምቤላም አሉ ወዘተ። ህወሓት ሊገዛ የቻለውና የሚችለው ሌሎችን በማባበልና በጥቅም በመደለል፤ የስልጣን አጋር ናችሁ በማለት፤ እኔ ከሌለሁ "ጠላቶቻችሁ" የቂም በቀል ዘመቻ ያካሂዱባችኋል ወዘተ በማለት ነው። "ኦሮሞውን አማራው ተመልሶ ስልጣን ይዞ ይጨፈጭፍሃል። አማራውን ወዮልህ፤ ኦሮሞው ስልጣን ከያዘ ማባረር ብቻ ሳይሆን በጅምላ ይጨፈጭፍሃል። ትግራዩን አማራውም፤ ኦሮሞውም አይምርህም" እያለ ህዝብ በፍርሃት ዓለም እንዲኖር አድርጎታል። ይኼ ሁኔታ በጋራ ጥቅም ምክንያት የጋራ አፈና እንዲካሄድ ረድቷል። ከላይ እንዳሳየሁት፤ የፖለቲካው አመራር በዚህ መልክ ከቀጠለ እድገትም ቢኖር የእድገቱ ውጤት የሚጠቅመው ጥቂቶችን ነው። ሌላው ቀርቶ ገዢው ፓርቲ ከስራ የሚወጡትን ባልደረቦቹንና በጡሮታ የሚወጡትን ተንከባክቦ ይይዛል።

በጡሮታና በሌላ ምክንያቶች የሚወጡ ግለሰቦች ራሱ መንግሥት የሚሰጣቸው የጡሮታ አበልና ድጎማ ወይንም ፓርቲው በሚቆጣጠራቸው ድርጅቶች የሚሰጣቸው ስራ--ለምሳሌ፤ የቦርድ አባልነትና ሊቀመንበርነት ተደማምረው የሚያሳዩት የገቢና የኃብት ክምችቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን ነው። በአሜሪካ የመካከለኛው መደብ ሰርቶ የሚያገኘው ወደ ታች እየወረደ ሲሄድ

የአንድ በመቶው ክፍል (The One Percent Rich and Superrich) ተብሎ የሚታወቀው መድብ የበለጠ ኃብት አከማችቷል። ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው የገቢና የኃብት ስርጭት ሁኔታ በኢትዮጵያ በባሰ ደረጃ ይከሰታል የሚል እምነት አለኝ። አበበ ሃይለ ባቀረበው መረጃ መሰረት እያንዳንዱ የህወሓት፤ ኢህአዴግ ሚንስትር ጡሮታ ሲወጣ ወይንም ስትወጣ መንግሥት **“በመቶ ሚሊየን ብር ወጭ** ተደርጎ ከፍተኛ ቪላዎች ከነ መዋኛ ገንዳው ሊገነባላቸው ከወሰነ” እውነትም አገዛዙ በጥቅም ላይ የተመሰረተ እንጅ የድሃውን ሕዝብ ገቢና ህይወት ለማሻሻል፤ የአገሪቱን እድገት ለማጠናከር፤ የመካከለኛ መደብ መሰረት እንዲይዝ ለማድረግ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አያስቸግርም። ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነቀርሳ ነው የሚል እምነቴ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም፤ በድሃው ሕዝብ ላይ የሚካሄድ ንግድ መቆም አለበት። አበበ ሃይለ “ይህች ህዝብ በጉጉት የተከታተላት የመልካም አስተዳደር ችግር የመፍታት ውይይት ወደ ተግባር ተቀይራ የህዝቡን እንባ የምታብስበት እለት በጉጉት እየተከታተለች መሆኑን መንግሥት አውቆ ተግባራዊ እርምጃ እንዲጀምር የበኩሌን ምክር እሰጣለሁ” ያለው ምክርና ምኞት ስኬታማ የሚሆን አይመስለኝም።

ለማጠቃለል፤ ኢትዮጵያ የምትከተለው አድሏዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መርህ (Crony Capitalism) የጥቂቶች አገልጋይ መርህ ነው። “ፈጣን እድገት አለ ዳቦ የለም” የሚለውውን ብሂል ስለሚያንፀባርቅ፤ ተከታታይና ፍትሃዊ እድገትን ትርጉመ ቢስ ሆኗል። ችግሩ በማባበል፤ በዲስኩር፤ በግምገማ ወዘተ የሚፈታ አይደለም። ገዢው ፓርቲ ስለመልካም አስተዳደር የፈለገውን ጥናት፤ ምርምርና ውይይት ቢያደርግ እመርታዊ የሆነ የስርዓትና የመዋቅር ለውጥ አይቻልም። ተጠቃሚዎቹ አይፈቅዱም። የፖለቲካ ለውጥ ካልተደረገ የገንዘብና የኢኮኖሚ አመራር ለውጥ አይቻልም።